# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

17




ታኅሣሥ ፴—፲፱፻፸፱ ዓ. ም.

**ለውይይት መነሻ**

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቍጥር ፩ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው።

# ስለ መንግሥት

### ፲፪ኛ ትምህርት ከን.ዓ.

ኅብረተሰብ ነክ ከሆኑ ጉዳዮች ሁሉ እንደመንግሥት ጉዳይ የተጭበረበረ ጥያቄ ያለ አይመስለንም ። የከበርቴ አፈ ቀላጤዎች መንግሥት የሚባለውን ድርጅት ለመላው ኅብረተሰብ ጥቅምና ደኅንነት የቆመ ከመላው ኅብረተሰብ ፈቃድ ወይንም ከመለኮታዊ ፈቃድ የመነጨ በኅብረተሰቡ ውስጥ እገሌ ተእገሌ ብሎ ሳያዳላ ለሁሉም እኩል የቆመ የማያዳላ ድርጅት አድርገው ያቀርቡታል። ከዚህም አያይዘው መንግሥት ከዚህ በፊት ለዘለዓለም የኖረና ወደፊትም ለዘለዓለም የሚኖር ድርጅት አድርገው ያቀርቡታል ።

ባጭሩ « መንግሥት አያዳላም ። ዘለዓለም ነበር ። ዘለዓለም ይኖራል» ይባላል ። በማርክሲዝም አስተሳሰብ ግን ይህ በፍጹም ትክክል አይደለም። አንደኛ በማርክሲዝም አስተሳሰብ መሠረት መንግሥት የሚባለው ድርጅት ከማዳላትም አልፎ አንዱ መደብ ሌላውን መደብ ጨቁኖ የሚገዛበት የማስገደጃ መሣሪያ ነው ። ሁለተኛ ደግሞ መንግሥት የመደቦች መሣሪያ እንደመሆኑ መጠን የተወለደው ከመደቦች ጋር አብሮ ነው ። መደቦች ባልነበሩበት ኅብረተሰብ መንግሥት የሚባለው የማስገደጃ ድርጅት አልነበረም ። ወደፊትም መደቦች በሚጠፉበት ኅብረተሰብ ውስጥ መንግሥት የሚባለው ድርጅት አይኖርም ።

ኅብረተሰቦች በመደብ መከፈል ሲጀምሩ የመደቦች ትግልም አብሮ እንደተወለደ ተመልክተናል ። የባሪያ ገዢዎች ሥርዓት ሥር እየሰደደ ሲሔድ ባሪያ ገዢዎች ባሮችን ጨቁነው ለመግዛት ከሕዝቡ የተነጠለ ሠራዊት ፣ ፖሊስ ፣ ቢሮክራሲ ፣ ዳኛ ፣ ፍርድ ቤትና ወህኒ ባጭሩ በተቀነባበረ ዘዴ ጥቅማቸውን ሊያረጋግጥ የሚችል የማስገደጃ መሣሪያ አስፈለጋቸው ። ይህ መንግሥት የተባለ ድርጅት አንዱ መደብ ሌላውን ጨቁኖ ለመግዛትና የመደብ ጥቅሙን ለማረጋገጥ የፈጠረው የማስገደጃ ድርጅት ነው ።

በማርክሲዝም አስተሳሰብ እንግዲህ መንግሥት ማለት አንዱ መደብ ሌላውን መደብ ጨቁኖ የሚገዛበት የማስገደጃ መሣሪያ እንጂ ከመደቦች ትግል ውጭ ፣ ከመደቦች ትግል በላይ ያለና የማያዳላ አካል አይደለም ።

በአመጣጡም የተመለከትን እንደሆነ የምናየው ሐቅ ይኸው ነው ። መደቦች ባልነበሩበት በጥንቱ የጋርዮሽ ኅብረተሰብ ውስጥ እርግጥ የጋራ የሆኑትን ጉዳዮች ለመፈጸም ብቁ ለሆኑ በተለይ ተፈጥሮአዊ በሆነው የሥራ ክፍፍል መሠረት ለሽማግሌዎች የተተወ ያስተዳደር ተግባር ነበር ። ግን ይኸ አስተዳደር የመንግሥት አስተዳደር አልነበረም ። የጥንቱ አስተዳደር በችሎታቸው በተመረጡ ሰዎች የሚካሔድ አስተዳደር ሲሆን ፣ የሚያስከብሩትና የሚሠሩበት መመሪያ የመላ ኅብረተሰቡን ጥቅም ያረጋግጣል ተብሎ ሁሉም የሚያምንበት መመሪያ እንጂ ጥቂቶች ከጠቅላላው ኅብረተሰብ ፈንጠር ብለው ያወጡት ሕግ አልነበረም ። ይህንን ሕግ የሚያስከብሩባቸው ከሕዝብ ተለይተው የሚቋቋሙ ሠራዊት ፖሊስ ፣ ዳኛ ፣ ፍርድ ቤት ፣ ወህኒ ቤት ፣ ወዘተ . . . የመሳሰሉ አካሎችና ድርጅቶች አልነበሩም ።

እንግዲህ ይህ መንግሥት የሚባለው የማስገደጃ ድርጅት ከጥንቱ አስተዳደር የሚለይበት የመጀመሪያው ነገር ከሕዝቡ ተለይተው የሚሠሩ የማስገደጃ አካሎች ማለትም ፖሊስ ፣ ዳኛ ፣ ሠራዊት ቢሮክራሲና የማስገደጃ ድርጅቶች ማለትም ፍርድ ቤት ፣ ወህኒ ቤት . . . የመሳሰሉትን አቀነባብሮ በመያዙ ነው ።

በተጨማሪም የቀድሞው አስተዳደር የተደራጀው በቤት ዘመድ አካባቢ እንጂ በክፍለ ሀገር ወይም በግዛት ክፍፍል ላይ ተመሥርቶ አልነበረም ። መንግሥት የሚባለው የማስገደጃ መሣሪያ ግን በአንድ ቤት ዘመድ አካባቢ ሳይሆን በተወሰነ ግዛት ክልል ላይ የተመሠረተ አስተዳደር ሆነ ።

መንግሥት የማስገደጃ መሣሪያ ነው ስለተባለ መንግሥትን ሁልጊዜ በሁሉ ቦታ መቃወም ያስፈልጋል ወይ ? አያስፈልግም ። ይህ የሥርዓተ አልበኞች ዘይቤ ነው ። ሥርዓተ አልበኞች እንደ ማርክሲስቶች መንግሥት አንዱ መደብ ሌላውን መደብ ጨቁኖ የሚገዛበት የማስገደጃ መሣሪያ እንደሆነ ያምናሉ ። ነገር ግን ማርክሲስቶች መንግሥትን ገና ለገና የማስገደጃ መሣሪያ ነው ብለው አይቃወሙትም ። እንዲያውም መደቦችና የመደቦች ትግል እስካሉ ድረስ ጭቁን መደቦች በዝባዦችን ከሥልጣን ካወረዱ በኋላ እነዚህ ከሥልጣን የተፈናቀሉ በዝባዦች ተመልሰው እንዳያንሠራሩ ለማድረግና እነሱንም ለመደምሰስ የቀድሞ ተበዝባዥ መደቦች የራሳቸውን ጥቅም የሚያረጋግጡበት የማስገደጃ መሣሪያ ወይም መንግሥት ያስፈልጋቸዋል ። ሥርዓተ አልበኞች ግን ወደመደብ አልባ ሥርዓት በሚደረገው የሽግግር ዘመን የቀድሞ ጭቁኖች የራሳቸው የማስገደጃ መሣሪያ ወይም ፈላጭ ቆራጭ የሆነ መንግሥት እንደሚያስፈልጋቸው አያምኑም ። ይህ የመንግሥትን ታሪካዊ አስፈላጊነት የሚክድ የአናርኪስቶች አስተሳሰብ ዞሮ ዞሮ በሕዝባዊ አብዮት ተፈንግለው የወደቁት የቀድሞ በዝባዦች ተደራጅተውና ታጥቀው ተመልሰው ሥልጣን እንዲይዙ የሚያግዝ ፀረ ሕዝብ አስተሳሰብ መሆኑ ግልጽ ነው ።

እንግዲህ ማንኛውም መንግሥት ስሙ ፣ አጠራሩ ፣ መዋቅሩ የተለያየ መልክ ይያዝ እንጂ የመደቦች መሣሪያ እንደሆነ ግልጽ ነው ። እስካሁን በታሪክ ከታዩት መንግሥታት የጥቂት በዝባዦችን የበላይነት ያጸደቁት ሦስት ዓይነት መንግሥታት ሲሆኑ ፣ እነሱም የባሪያ ገዢዎች መንግሥት የፊውዳል መንግሥትና የከበርቴ መንግሥት ናቸው። እነዚህ መንግሥታት የተለያዩ ስሞችና ቅርጾች ቢወስዱም የመጀመሪያው የቆመው የባሪያ ገዢዎችን ጥቅም ለማረጋገጥ ፣ ሁለተኛው የቆመው የፊውዳል መደብን ጥቅም ለማረጋገጥና ሦስተኛው ደግሞ የቆመው የከበርቴውን መደብ ጥቅም ለማረጋገጥ ነበር ። በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ብዙኃኑን ወክሎ በቀድሞ በዝባዥ መደቦች ላይ ፈላጭ ቆራጭ የሆነ ሥርዓት ያሰፈነው የሶሻሊስት መንግሥት ነው ። ከዚህ ሥርዓት በፊት ግን የነበሩት መንግሥታት እርግጥ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም የቆምን ነን እያሉ ቢለፍፉም የበዝባዥ መደቦች አባላትን ጥቅም ለማስጠበቅ የቆሙ እንደሆኑ ግልጽ ነው ።

እርግጥ እነዚህ ሁሉ መንግሥታት ለመላው ሕዝብ ጥቅም የቆምን ነን ብለዋል ። አሁንም እነዚህ መንግሥታት ለሕዝብ ጥቅም የቆሙ ናቸው ይባላል ። ነገር ግን በመደቦች በተከፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ «ሕዝብ» የሚባለው ቃል ራሱ ከታሪክ ጋር የተለያዩ ይዘቶች ይኖሩታል ።

ለምሳሌ የጥንቱን የግሪክ መንግሥት እንውሰድ ። ይህ መንግሥት የተመሠረተው በባሪያ ሥርዓት ላይ ነበር ። ስለሆነም መንግሥቱ የባሪያ ገዢዎችን ጥቅም ለመጠበቅ የቆመ መንግሥት ነበር ማለት ነው ። እርግጥ በዚያን ጊዜ በግሪክ የነበረው መንግሥት «ሪፑብሊክ» ወይም ሕዝባዊ መንግሥት መባሉ ሊያደናግር ይችላል ። በእርግጥም ያ መንግሥት በሕዝብ የተመረጠ ፤ ለሕዝብ የቆመ በሕዝብ የሚሻር በዲሞክራሲ የሚሠራ መንግሥት ነበር ። ነገር ግን በዚያን ሥርዓት «ሕዝብ» የሚባሉት የገዢው መደብ አባላት እንጂ ብዙኃኑና በባርነት ተጨቁነው ይኖሩ የነበሩት ዜጎች አይደሉም ። እነዚህኞቹ ተጨቁነው የሚኖሩና ማንኛውም ዓይነት ሰብአዊ ዲሞክራሲያዊ መብት የተነፈጋቸው እንዲያውም ከሰው ሳይሆን «ከሚናገር መሣሪያ» የሚቆጠሩ ነበሩ ።

በፊውዳሉም ሥርዓት የሔድን እንደሆነ የፊውዳሉ መንግሥት እርግጥ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም የቆምኩ ነኝ ቢልም «ሕዝብ» ብሎ የሚጠራውና ጥቅሙን የሚጠብቅለት የፊውዳሉን መደብ እንደሆነ ግልጽ ነው ። በከበርቴዎች ሥርዓት የተቋቋሙትም መንግሥታት ከመላ ሕዝብ ምርጫ የፈለቁ ስለሆኑ ጠቅላላውን ሕዝብ እንወክላለን ለማለት ይሞክራሉ ። ነገር ግን የመደብ ይዘቱ እንጂ አንድን መንግሥት ከሕዝብ መመረጡ ብቻ በእውነት ለሕዝብ የቆመ መንግሥት አያደርገውም ። በእኛ አገር እንኳን ብንሔድ በቀድሞው ሥርዓት ውስጥ «የሕዝብ ወኪል» ተብለው የተመረጡ እንደራሴዎች ያሉበት ፓርላማ ነበረን ። ነገር ግን ለቀድሞው ሥርዓት የፓርላማ አባላት የሚባሉት ገንዘብና መሬት ያላቸው ፤ ወይም ደግሞ ገንዘብና መሬት ባላቸው ሰዎች ድጋፍ ላይ ተመርጠው የመጡ የገዢው መደብ አባላት ወኪሎች እንጂ የአብዛኛው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ወኪሎች አልነበሩም ። በካፒታሊስት አገሮችም ብንመለከት ፤ እርግጥ የመንግሥቱ መሪዎች የሚመረጡት በሕዝብ ነው ። ነገር ግን የሬዲዮ ፤ የጋዜጣ ፤ የቴሌቪዥንና የመሳሰሉት የሕዝብን አስተሳሰብ ለማነጽ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች እንደተቀሩት የምርት መሣሪያዎች በከበርቴዎች እጅ ናቸው ። ስለዚህ ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ ከሁሉ የመመረጥ ዕድል ያለው ፤ ባለው የገንዘብ ኃይል አማካይነት እነዚህንና ሌሎችም የመገናኛ ዘዴዎችን በሚገባ ሊጠቀምባቸው የሚቻለው ክፍል ነው ። ይህ ክፍል ደግሞ የሠርቶ አደሩ መደብ ሳይሆን የከበርቴው መደብ እንደሆነ ግልጽ ነው ።

መንግሥት በእርግጥ የመደቦች መሣሪያ መሆኑን ለማየት ከእርሱው ጋር በጥብቅ የተያያዘውን የሕግን ጉዳይ ጠጋ ብሎ ማየት ያስፈልጋል ። የአንድ መንግሥት የማስገደጃ አካሎችና ድርጅቶች በሙሉ ዋና ተግባራቸው በልማድም ሆነ በጽሑፍ የተደነገጉትን ሕግጋት ማስከበርና ከነዚህ ሕጎች ውጭ የሚሠራውን ወይም እነሱን የሚቃረነውን ማንኛውንም ኃይል «ሕገ ወጥ» እያሉ አስፈላጊውን ርምጃ መውሰድ ነው ። ባጭሩ አንድ መንግሥት ዓላማው የተደነገጉትን ሕግጋት ማስከበር ነው ። ስለዚህ ሕግ የሚባለው ነገር የመደብ ይዘት እንዳለውና ለአንድ መደብ የሚያዳላ መሆኑን በማሳየት በቀላሉ መንግሥት የሚባለውም ድርጅት የመደብ ይዘት እንዳለውና እንደሚያዳላ ለመረዳት ይቻላል ። ስለሆነም በሕግና በመንግሥት መሐከል ያለውን ግንኙነት እንመልከት ።

( ይቀጥላል )